# መቅድም

ከልጅነቴ ጀምሮ፣ ሁኔታዬ ላይ የተለየ ነገር እንዳለ ሆኖ ይሰማኝ ነበር። ስለዚህ ያሚያጋጥሙኝን ነገሮች መዝግቤ መያዝ ፈለግሁ። እናም ማስታወሻዎች መጻፍ የጀመርኩት በአሥራ አንድ ዓመቴ ነበር። ነገር ግን “የምተርከው ታሪክ አለኝ” የማለት እምነት አልነበረኝም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ ብዙ ባህሎችን፣ ቋንቋዎችን፣ ኃይማኖቶችንና ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎችን ማወቄን ስገነዘብ፤ አንድ ነገር ለማድረግ ወሰንኩ። ይህንን የሕይወቴን ውጣ ውረድ መጽሀፍ ለመጻፍ ወሰኜ ሳስስብ፤ ጥቂት መሰናክሎች አጋጥመውኛል። የቋንቋ እጥረትና ስሜትን ማፈን። የጥፋተኝነት ስሜትና ያለፈውን ሁሉ ማስታወስን መፍራት። ምንም ማሻሻል የማይቻልበት ሁኔታም ተፈጠረ።

## ቋንቋ

በሦስት ቋንቋዎች መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እችላለሁ። ሌሎች ሁለት ቋንቋዎችም እሞክራለሁ። የትውልድ ሀገሬን ወይም የአፍ መፍቻ ቋንቋዬን ከተጠየቅኩ ግን ቀጥተኛ መልስ ለመስጠት እቸገራለሁ። የመናዊ ነኝ፣ ዐረብኛም እናገራለሁ ብል ጥርት ያለ ዐረብ እንደሆንኩ ልቆጠር እችላለሁ። ግን አይደለሁም። አማርኛ የምችል ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለትም የእኔን ማንነት በምለዓት አያሳይም።

ከሁሉም አስቀድሞ የተማርኩት ቋንቋ በመሆኑ ዐረብኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋዬ ሊወሰድ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ አምስት ዓመት ሳይሞላኝ አማርኛና ኦሮሚፋ ተምሬአለሁ። በዚህ ላይ ገና ድክ ድክ ስል አባቴ አንዳንድ የእንግሊዘኛ ቃላት አስጨብጦኛል። ትምህርት ቤትም እንግሊዝኛ ቀስሜአለሁ።

በእኔ ዕድሜ በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት መሠረት ማንኛውም ሰባተኛ ክፍል የደረሰ ተማሪ፤ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች የሚማረው በእንግሊዝኛ ነበር። በመደበኛው የአማርኛ ትምህርቴ ወቅት ግእዝን ደርቤ ለመማር ችያለሁ።

በእነዚህ ምክንያቶች "ስንት ቋንቋ ትናገራለህ" ተብዬ ስጠየቅ ቁርጥ ያለ መልስ መስጠት ያውከኛል። አራት? አምስት? እንዲያውም አራት ተኩል ማለቱ ሳይቀለኝ ይቀራል?... እውነታው ግን እስከ ዛሬ ድረስ በየትኛዎቹም ቋንቋዎች ትውስታዬን ያለመጻፌ ነው።

በእንዲህ ያሉት ሳንካች ሳላመሃኝ ታሪኬን ለመጻፍ ወሰንኩ። የመጀመሪያውን ቅጽ ያነበቡት ሁለቱ ልጆቼ "አባባ መጽሐፍህ ብዙ መረጃዎች ይዟል፣ ስሜት ግን ያንሰዋል" አሉኝ። ለካንስ ያለፈ ዘግናኝ ሕይወቴን ከእነገፈቱ ከማካፈል ይልቅ መረጃ የሚያቀብል ተራ ዘጋቢ ኖኜ ኖሯል።

ታሪኬን አንባቢ እንዲመሰጥበት ማድረግ እንዴት ይቻለኛል? የተዋበ ጭውውት፣ ማራኪ ገፀ-ባህሪያት እና አጓጊ ፍሰት ያለው ታሪክ እንዲሆን ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል?" ስል ራሴን ጠየቅኩ፡ ፡ የጎዳና አሰቃቂ አፍ የዋጠው የስምንት ዓመት ልጅ ያቆራመደውን ፍርሐት፣ ስቃይ፣ ተስፋቢስነት፣ አለኝታ ማጣት ... የሚገልጹ ኮስታራ ቃላት ሊኖሩ ይቻላሉ የሚል ግምት አልነበረኝም። በግልጽነት፣ በታማኝነት፣ በሚዛናዊነት ለማቅረብ የምፈልገውን

ትውስታዬን የትና እንዴት መጀመር እንዳለብኝ አላውቅኩም ነበር።

## ራስ ወቃሽነት

በዚህ ጥንቅር ውስጥ የተጠቀሱ ሰዎች (የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች) ቅር እንዳይሰኙብኝ መጨነቄ አልቀረም። ባደግኩበት ባህል ውስጥ የማይደፈሩ አይነኬ ጉዳዮች በታሪኬ ከአለፍ ገደም ተጠቃቅሰዋል። ያደግኩበትን ባህልና ወግ እንዳልነካ እየተጠነቀቅኩ፤ ኃይማኖታዊውን ድንበር ለመጣስ ዳር ዳር እያልኩ መሆኔን ሳስበው ስጋት ብጤ ይጎነትለኛል።

ዓላማዬ ቤተሰቤን ማሳፈርና ማሸማቀቅ ሳይሆን ከምንም በላይ ለራሴና ለአንባቢዎቼ ታማኝ መሆን ነው። የቱንም ያህል ብፈራና ብቸርም ከታሪኬ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዕይታዎች በመጽሐፌ ቅጠሎች ሁሉ ማነሳሳቴ አልቀረም።

የታሪኬ አንጓዎች ተገጣጥመው መነበብ አለባቸው። አንባቢዎቼ ከተለያየ ማኅበራዊ ዳራ የበቀሉ የግል፣ የማኅበረሰብና የፖለቲካ ጉዳዮችን ይቃኙ ዘንድ፤ አንዳንድ ተንኳሽ አለያም አይነኬ ጉዳዮችን መንካቴን አልክድም።

## ስጋት

በብዙ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የነበሩኝን ሕመሞችና ቅሬታዎች ተላምጄአቸዋለሁ… ከክፉ ትዝታዬ ጋር እርቅ ፈጥሬአለሁ… የሚታየኝም ይኸው ነው። ዳሩ ግን እንዴት ነው ራሴን

የምገልጸው? የገዛ እኔነቴን በመስተዋት ውስጥ ሳየው ምንድን ነው የምመስለው?

ይህ እንዲሆን ከውስጣዊ ነፍሴ ቋት ውስጥ በጥቂቱ እየቆነጠርኩ ለብዙኃኑ አንባቢ ማቋደስ ሊኖርብኝ ነው። እስከዛሬ ድረስ የግል ምሥጢሬ የነበሩና ማንም የማያውቃቸው የማንነቴ ሰበዞች እየተነቀሱ ያለ ስስትና ንፍገት ተዘርዝረዋል። እንግዲህ ከዚህ በኋላ በዓለም መድረክ ተዘርግቻለሁ። ውስጤን አደባባይ አስጥቻለሁ። ጥልቅ ስሜቴንም ሆነ የግል ታሪኬን ገላልጬ የማሳየት ሐሳብ፤ በራሱ አስፈሪ ነው። ይህን ጥልቅ ማንነት አውጥቼ በመዘርገፌ፤ ውስጤ ባዶ ሆኗል። ቀለል ብሎኛል።

ይህን መጽሐፍ በቅጡ መሰነድ የማይገፉቱን ተራራ መውጣት… በማያሸነፉት የጦር አውድማ መዋደቅ… መሆኑን አውቃለሁ። ድጋፍ አስፈለገኝ። ደግሞም ከእኔው እኩል የሚተጉ ሁነኛ አጋሮች አጋጠሙኝ።

ለዚህ ሥራዬ የቀኝ እጅ የሆኑኝን የሥነ-ጾሑፍ ተጠባቢያን ላስተዋውቃችሁ፤

የታሪኬ ባለቤት እኔ ነኝ። በገደ ቢስ ሕይወቴ የተጎሰምኩት እኔው ራሴ ነኝ። በውል አስረግጬ የምናገረው ቁስልና ድል ያዥጎረጎረው ማንነት አለኝ። ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ባለቤቶች የተጠቀሱት አጋሮቼ ጭምር ናቸው። ከእነርሱ ያልተገደበ ተሳትፎ ውጪ ጥረቴ ከንቱ ነበር።

ብዙም የምሰጠው ስለሌለኝ አንዳች የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ብለው አልሠሩትም። “ይህ ታሪክ ለሌሎች የሚያቀብለው ቁም ነገር አያጣም” በሚል ቅን ልቦና ተነሳስተው የተሳተፉ ናቸው።

"ጸሐፊ ከሚስላቸው ፊደላት በሚያፈልቀው ጥዑም መዐዛ የተደራሲውን አፍንጫ የሚያፍነከንክ ጠቢብ ነው።" የሚል እምነት አለኝ። አትክልቶቼ ያብቡ ዘንድ ውኃ ያጠጡልኝ እነዚህ ቀኝ እጆቼ ናቸው። እነሆም መጽሐፌን ለእነርሱ በምሰጠው ምስጋና ልባርከው።